# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

## የዕለቱ ምስባክ

ሐወፅካ ለምድር ወአርወይካ
ወአብዛህኮ ለብዕላ
ፈለገ እግዚአብሔር ምሉዕ ማያት

ምድርን ጐበኘሃት አጠጣሃትም
ብልጥግናዋንም እጅግ አበዛህ
የእግዚአብሔር ወንዝ ውኃን የተመላ ነው።

መዝ ፷፬፥፱

ወንጌል፥ ማቴ ፵፫፥፵፭
ቅዳሴ፥ የኤጲፋንዮስ ቅዳሴ (ዐቢይ)

## የዕለቱ ትምህርት

## በጻድቃንና በኃጢአተኞች ላይ ዝናምን ያዘንማል።

ቅዱስ ወንጌል በቅዳሴ ጊዜ ሲነበብ እንደሰማነው «ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህን ጥላ» በሚለው ሕግ ኦሪት መሠረተ ክፋዎችን አትጥሉ «በሰማይ ያለው የአባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሙአችሁን መርቁ፤ ለሚጠሉአችሁ መልካም አድርጉ ለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፉዎችና በበጐዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፤ በጻድቃን እና በኃጢተኞችም ላይ ዝናምን ያዘንማልና የሚወዱአችሁንማ ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ … የሰማይ አባታችሁ (በቸርነት ሁሉን በመመገብ) ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍጹማና ሁኑ» በማለት በክረምት እግዚአብሔር በሚሰጠን ዝናም አመሳስሎ ፍቅርን ያስተምረናል።

ዳዊት እንደዘመረው፤ ዲያቆኑም ሲሰብክ እንደሰማችሁ እግዚአብሔር ለሁሉም ምድርን የዘሩባትን እንድታበቅል በበረከቱ ይጐበኛታል፤ በፍሬም ያበለጽጋታል፤ የይቅርታው ወንዝ የምሕረት ውሃ የተሞላ ነው (መዝ ፷፬፥፱)። ይህም የሆነው ለሚያምነውም ለማያምነውም ለኃጥኡም ለጻድቁም ለሁሉም ነው እንጂ ለአንዱ እንደዚህ ለሌለው ደግሞ እንደዚያ አይደለም። ቅዱስ ጳውሎስም በገላትያ መልእክቱ «ሰው የዘራውን ሁሉ ያንኑ ያጭዳል በገዛ ሥጋው የሚዘራ በሥጋ መበስበስን ያጭዳል፤ ባንዝልም በጊዜው እናጭዳለንና መልካም ሥራን ለመስራት አንታክት እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ለሰው ሁሉ፤ ይልቁንም ለሃይማኖት ሰዎች መልካም እናድርግ» በማለት በክረምት ከሚዘራው በበጋም የዘራውን ከሚያጭደው ገበሬ ጋር አመሳስሎ ይቅርታን፤ በጐነትን ይሰብክልናል።

በረዳቱ ዲያቆን የተነበበው (፪ኛ ጴጥ ፪፥፩-፲) ያለው ቃልም ለሁሉ እንደሥራው እግዚአብሔር ዋጋ እንደሚሰጥ በቅድስና ሕይወቱን ለያዘው ሕይወቱን እንደሚያድል በሰውነቱ ላይ ዝሙትን፣ ጥልን የሚዘራም ሞት ይከፈለዋል ካለ በኋላ፤ ርኩሳን መናፍስትን እና የተፈረደባቸውን ሰዎች እንደምሳሌ ይጠቅስልናል።

## የክረምት ሦስተኛ ሰንበት

ከሰኔ ፳፮ እስከ ሐምሌ ፲፮ ቀን ድረስ በዐተ ክረምት (የክረምት መግባት) ይባላል። ሥርዓተ አምልኮውም የተመሰረተው ወቅቶችን ስለሚለውጠው አምላክ ኃይል፣ ስለ ደመናዎች፣ ስለ ዘር፣ እግዚአብሔር በጋውን አሳልፎ ክረምቱን ስለማምጣቱ፣ ደረቁን ስለማለምለሙ በሚያስታውሱ ክፍላተ መጽሐፍት ላይና መዝሙራት ላይ ነው። በተጨማሪም በክረምት ነገረ ትንሣኤ ይሰበካል፤ የዘሩ መዘራት እንደ መሞት መቀበር፤ መብቀሉ ደግሞ እንደ መነሳት ይወሰዳል። በምሳሌ ይሰበካል ክረምት ቢዘገይም እንደማይቀር ምጽአትም ሞትም እይቀሩምና በንጽጽር ይሰበካል።

### የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

ንጉሥ ውእቱ ክርስቶስ
«ክርስቶስ ንጉሥ ነው»

### በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ገላ ፮፥፮-፲ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፪ኛ ጴጥ ፪፥፩-፲ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፲፯፥፳፪-፴፩ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

አንባቢ ሆይ፥ ቀጥ ብለህ የሰማዩን ደመና ተመልከት በዝናም ጊዜም የዝናምን አወራረድ ልብ በል። እግዚአብሔር አባትህ በሁሉም ላይ ደመናውን ይጋርዳል፤ ዝናምንም ለሁሉ ያዘንማል። የክፉዎችን ሰፈር ለይቶ አይተወውም፤ አቅቶት ሳይሆን መግቦቱ የተስተካከለ ስለሆነ ነው። እርስዎም በክረምቱ የሰማዩን ደመና፤ የክረምቱን ዝናም አይተው እንደ አባትዎ ለሁሉም የፍቅር እና የርህራሄ ልብ ይኑርዎ።

በቸርነቱ ሁሉን ለሚመግብ ጌታ ክብር ይሁን … አሜን።

### ጥቅስ ከቅዱስ ያሬድ

ግእዝ፥ ንጉሥ ውእቱ ክርስቶስ መሐሪ ውእቱ ይሁብ ዘርዓ ለዘራዒ (አዝ)
ያሠምር እክለ ለሲሳይ ያነስአ እምድር ለነዳይ (አዝ)
ዘኢየሐይድዎ ስልጣኖ ዘይኤዘዝ ትፍሥህት ለጻድቃኒሁ (አዝ)
ወሰርአ ሰንበተ ለሰብእ ዕረፍተ ገባሬ ሕይወት ያርሁ ክረምተ በበዓመት ንጉሥ ውእቱ ክርስቶስ ንጉሥ ውእቱ ክርስቶስ።

ትርጉም፥ ክርስቶስ ንጉሥ ነው፤ ክርስቶስ መሐሪ ነው፤ ለዘሪ ዘርን ይሰጣል (አዝ)
እህልን ለምግብ ያስምራል፤ ደሃውን ከምድር ያስነሳዋል (አዝ)
ስልጣኑን የማይቀሙት ለጻድቃን ደስታን የሚያዝ፤
ሰንበትን ለእረፍት የሚሰራ፤ ክረምትን በየዓመቱ የሚያመጣ ክርስቶስ ንጉሥ ነው፤ ክርስቶስ ንጉሥ ነው (መዝሙር)

◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆

በግእዝ፥ በትእዛዙ ይቀውም ዕለት ወበቃሉ የአርጉ ደመናት ያወርድ ዝናማተ ያርሁ ክረምተ በበዓመት ውእቱ እግዚአ ለሰንበት

ትርጉም፥ በትዕዛዙ ዕለት (ቀን) ያጸናል። በትዕዛዙም ደመናዎች ዝናምን ያወርዱ ዘንድ ይወጣሉ፤ በየዓመቱ ክረምትን ያመጣል፤ እርሱ የሰንበት ጌታ ነው። (አራራይ)

ወስብሐት ለእግዚአብሔር … አሜን።

ከመምህር ልዑለ ቃል አካሉ ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ፩ኛ መጽሐፍ የተወሰደ
EthiOrthodox e-mail Outreach EthiOrthodox@AOL.COM